


# በቨርጂኒያ አዲስ ቀን ነው!

## የመኖርያ ፍቃድ (Green Card) ላላቸው ሰዎች የወጡ አዳዲስ የጤና ሽፋን ሕጎች!

### ምን አይነት የጤና ሽፋን ሕጎች ናቸው ለስደተኞች እየተቀየሩ ያሉት?

ከዚህ ቀደም፣ በአሜሪካ የሚገኙ  አምስት ዓመት እና ከዚያ በላይ በአሜሪካ የኖሩ የመኖሪያ ፍቃድ ያላቸው ሰዎች (ወይም ህጋዊ ቋሚ ነዋሪዎች በመባል የሚታወቁት) ከቨርጂኒያ ሜዲኬይድ የጤና ሽፋን ብቃት ለማግኘት የ40 ሩብ ዓመታት (10 ዓመታት) የሥራ ታሪክ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርባቸው ነበር፡፡ ይህ የሥራ መስፈርትመጋቢት 31, 2021 ላይ

### ያበቃል፡፡ይህ ምን ማለት ነው?




ከ ሚያዚያ 1፣ 2021 ዓ.ም ጀምሮ በአሜሪካ ለአምስት እና ከዚያ በላይ ዓመታት የኖሩ የመኖሪያ ፍቃድ ያላቸው ሰዎች (ህጋዊ ቋሚ ነዋሪዎች) ለቨርጂኒያ ሜዲኬይድ ነጻ ወይም ባለ-አነስተኛ ዋጋ የጤና ሽፋን ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡  አምስት ዓመቱ የሚጀምረው ወደ አሜሪካ ከገቡበት ዕለት አንስቶ ነው፡፡

### የቨርጂኒያ ሜዲኬይድ ምንድነው?

የ ቨርጂኒያ ሜዲኬይድ የተሟላ የጤና መድሕን ነው፡፡ ይህም ሀኪም ጋር ለምርመራ መቅረብን፣ የመድሀኒት ትዕዛዞችን፣ ሆስፒታል ውስጥ ተኝቶ መታከምን፣ የጥርስ እንክብካቤን፣ እና ሌሎች ብዙ ነገሮችን ይሸፍናል፡፡

### እንዴት ማመልከት ወይም የበለጠ መረጃ ማግኘት እንደሚቻል፡

- የጋራ ድጋፍ (Common Help) በሚለው በቀጥታ በበይነ-መረብ ያመልክቱ **www.commonhelp.virginia.gov** ይጎብኙ**www.coverva.org** *ወይም* **www.cubrevirginia.org**
- ከአካባቢያዊ አሳሽዎ ወይም የማመልከቻ አጋዥዎ ጋር **www.coverva.org/findhelp/** *ወይም***https://www.cubrevirginia.org/findhelp/***ወይም እዚህ ላይ ይደውሉ* **1-888-392-5132**
- ወደ Cover Virginia Call Center የጥሪ ማዕከል በ **1-855-242-8282** (TDD:  1-888-221-1590) በስልክ ለማመልከት ይደውሉ፣ ከሰኞ - ዓርብ: ከጠዋቱ 8:00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 7:00 ሰዓት ወይም ቅዳሜ፡ ከጠዋቱ 9:00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12:00  ሰዓት
- የወረቀት ማመልከቻ (በኢንግሊዘኛ ወይም በስፓኒሽ የተጻፈ) በፖስታ ይላኩ ወይም በአካባቢዎ ለሚገኘው Department of Social Services (የማሕበራዊ አገልግሎት መምሪያ) በአካል በመሄድ ያድርሱ። ቀጣዩን ድሕረ-ገጽ በመጎብኘት በአቅራቢያዎ የሚገኘውን የማሕበራዊ አገልግሎት መምሪያ ያግኙ፡ **dss.virginia.gov/localagency/**

**በሁሉም ቋንቋዎች የሚሰጡ የጽሁፍ እና የቃል ትርጉም አገልግሎቶች በ Cover Virginia (የቨርጂኒያ ሽፋን) በኩል 1-855-242-8282 ላይበመደወል ይገኛል፡፡**

***ጥገኝነት ጠያቂዎችን፣ ስደተኖችን፣ሕጋዊ ነዋሪነት ያለቸው ልጆችን፣ ነፍሰ-ጡር ሴቶችን፣ ከውጭ ሃገር የመጡ ነዋሪዎችን እና ድንገተኛ ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሌሎች ብቁ የሆኑ የአገሪቱ ዜግነት የሌላቸውን ጨምሮ፣  የጤና ሽፋን የማግኛ ሌላ መንገዶች አሉ፡፡ ብቁ መሆንዎን ለማረጋገጥ ቢያመለክቱ ጠቃሚ ነው!***

COVER VIRGINIA
Connecting Virginians to Affordable Health Insurance

VIRGINIA'S MEDICAID PROGRAM
DMAS